


## ጳውሎስ በአገረ ገዢዎች ፊት

- ጳውሎስ በሶስት አገረ ገዢዎች ፊት ቀረበ።
  ቀላውዴዎስ ሉስዮስ በመባል የሚታወቀው ሻለቃም ፊሊክስ ለሚባለው አገረ ገዢ ደብዳቤ ላከ። በደብዳቤውም በእርሱ ላይ የቀረቡትን ክሶች ዘርዝሯል። ከአምስት ቀን በኋላም የአይሁድ መሪዎች ከጠበቃቸው ጠርጠሉስ ጋር መጡ። ጠርጠሉስም የአይሁዳውያንን የክስ ጭብጥ አስረዳ። ጳውሎስም የክስ መቃወሚያውን አቀረበ። አገረ ገዢው ፊሊክስ ጳውሎስን ለሁለት አመታት በእስር ቤት አቆየው። በዚህ ጊዜም ከእስር ቤት እያስላከ ያስመጣውና ያወያየው ነበር።

- ከዚህ በኋላም ጳውሎስ ጶርቅዮስ ፊስጦስ በሚባለውና በፊሊክስ ቦታ በተተካው አገረ ገዢ ፊት ቀረበ። አሁንም በጳውሎስ ላይ የቀረበው ክስ ተነበበ። ጳውሎስም የቀረበበትን ክስ ተቃወመ። ጳውሎስም በቄሳር ፊት እንዲቀርብና በዚያ ጉዳዩ እንዲታይለት አመለከተ። ማመልከቻውም ተቀባይነት አገኘ።

- ወደ ሮም የሚጓዝበት ጊዜ ከመቃረቡ በፊትም ንጉስ አግሪጳ ከሚስቱ በርኒቄ ጋር ወደቂሳሪያ መጣ። ፊስጦስም ስለጉዳዩ ከአግሪጳ ጋር ተወያየ። አግሪጳም ጳውሎስ የሚለውን ለመስማት ፈለገ።

- በተከታዩ ቀን ጳውሎስ ንጉስ አግሪጳ ፊት ቀረበ። ጳውሎስም እንዴት ሕይወቱ እንደተለወጠ በንጉስ አግሪጳ ፊት ተናገረ። ይኸውም ቀድሞ የክርስቲያኖች አሳዳጅ እንደነበርና አሁን ግን እርሱ ራሱ ክርስቲያን እንደሆነ ተናገረ። ፊስጦስም ንግግሩ የእብድ ንግግር እንደሚመስል ተናገረ። ጳውሎስም ለሁለቱ አገረ ገዢዎች ነገሩን በሚገባ ማስረዳቱን ቀጠለ።

- በመጨረሻም ሁለቱ አገረ ገዢዎች ክፍሉን ለቀው ወጡ። ጳውሎስን ለሞትም ሆነ ለእስር የሚያበቃው ምንም ወንጀል እንዳልፈፀመ ተስማሙ። አግሪጳም ጳውሎስ በቄሳር ፊት ጉዳዩ እንዲታይለት ይግባኝ ባይጠይቅ ኖሮ ይፈታ እንደነበር ተናረገ። እግዚአብሔር ጳውሎስ ወደ ሮም እንዲሄድ እንዳቀደና ወደሮም መጓዙ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያውቃል።

*ጳውሎስ በአገረ ገዢዎች የቀረበበትን ታሪክ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 23፡25 እስከ ምዕራፍ 26፡32 ውስጥ ማንበብ ይቻላል።*

http://gardenofpraise.com